804

# በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1983 የዘጠኝ ወራት

## የሥራ ክንውን ሪፖርት

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1983

# በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1983 የዘጠኝ ወራት

## የሥራ ክንውን ሪፖርት

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1983

# ማ ው ጫ

## አርዕስት


1. መግቢያ .............................. 1

2. የ1983 የስታቲስቲክስ ዐቅድ ይዘት ........... 2

3. የ1983 የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን ግምገማ .... 4

4. የበጀትና የሰው ሃይል አጠቃቀም ..............16

5. ያጋጠሙ ችግሮች ........................18

## 2. የ1983 የስታቲስቲክስ ኣቅድ ይዘት፣

በ1983 ለማካሄድ የታቀዱት የስታቲስቲክስ ሥራዎች ቦስት ዋና ዋና ይዘት ያላቸው ሲሆኑ ኣነሱም፡ —

2.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ፣

2.2 ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አጠናቅሮና አቀናብሮ ውጤቱን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ከዚሁም ጋር ተመሣሣይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን፣

2.3 በ1984 ይከናወናሉ ተብሎ ለሚታሰቡ ጥናቶችና ሥራዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ናቸው።

## 2.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ በተመለከተ፣

በ1983 ስታቲስቲካዊ ጥናቶችን በማካሄድ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በኣቅድ የተያዙት የጥናት ዓይነቶች ቀጥሎ በዝርዝር የተመለከቱት ናቸው።

1. የግብርና ስታትስቲክስ ጥናቶች፣
   - ሀ/ የሰብል ትንበያ ጥናት
   - ለ/ የኣርሻ ናሙና ጥናት
   - ሐ/ የሕብረት ኣርሻዎች ጥናት
   - መ/ የመንግሥት ኣርሻዎች ጥናት
2. ትላልቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የማዕድንና ኤሌክትሪክ ጥናት፣
3. የሕንጻ ኮንስትራክሽን ጥናት፣
4. የውጭ ንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ ጥናት፣
5. የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የመገራ ጥናት፣
6. የዋጋዎች ጥናት / በገጠርና በከተማ /፣
7. የቤተሰብ በጀት ጥናት / በከተማ /፣
8. የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት፣
9. የጤናና የአመጋገብ ጥናት፣
10. ብሔራዊ የአመጋገብ ክትትል ሥርዓት ጥናት፣
11. የአካባቢ ሁኔታ ጥናት፣
12. የማህበራዊ ጉዳይ ጥናቶች፣
13. የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የካርታ ሥራ ዝግጅት፣

14. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት፣ ሲሆኑ ከእነዚሁ መካከል በተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም አማካይነት ጥናቶችን በከተሞችም ለማካሔድ ታቅዶ አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ቢጠናቀቁም በበጀት እጥረት ምክንያት ዕቅዱን መሠረዝ ወይም ባልተወሰነ የዕቅዱ ዓመታት ማስተላለፍ ሁኔታው አስገድ ዷል።

2.2 <u>ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አጠናቅሮና አቀናብሮ ውጤቱን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ከዚህ ጋር ተመሣሣይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራ ዎች ማከናወን፣</u>

- በ1983 ወይም ከዚያ በፊት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጠናቀር አመቺ በሆነ መንገድ የቅንበርና የትንተና ሥራዎችን ማከናወንና የጥናቶቹን ውጤት የሚያመለክቱ ሪፖርቶችን ማውጣት፣
- በየዓመቱ ከሚካሄዱት ጥናቶችና ከልዩ ልዩ መሥሪያቤቶችና ድርጅቶች የሚሰበሰቡትን የተለያዩ የስታትስቲክስ መረጃዎች ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት በሚያመች መንገድ ማጠናቀር ማቀነባበርና ማዘጋጀት፣
- በተለያዩ መሥሪያቤቶችና ድርጅቶች የሚከናወነው የስታቲስቲክስ ሥራ ስለሚጠናከርበትና አሠራራቸውንም በማዕከላዊነት ለመምራትና ለመቆጣጠር ስለሚቻልበት ሁኔታ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣
- የስታቲስቲክስ ሥራን በሚመለከት ለልዩ ልዩ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የቴክኒክ ኣርዳታና ድጋፍ መስጠት፣

2.3 <u>በ1984 ይከናወናሉ ተብለው ለሚታሰቡ ጥናቶችና ሥራዎች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ በተመለከተ፣</u>

በ1984 ለሚካሄዱ ጥናቶችና ለሚከናወኑ ሌሎች ሥራዎች አስፈላ ጊው ቅድመ ዝግጅት በ1983 የሚካሄድ ይሆናል።ከሚካሄዱት ቅድመ ዝግጅ ቶችም መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች የተገለፁት ናቸው።

- በየጊዜው ከሚካሄዱት ጥናቶችና ቆጠራዎች ልምዱን በማዳበር የሚቀጥሉት ጥናቶችና ቆጠራዎች ሊካሄዱ ስለሚችሉበት ሁኔታ የአሠራር ዘዴዎችን በማሻሻል መቀየስ፣
- በ1984 ሊካሄዱ ለታቀዱ አዳዲስና ተከታታይነት ላላቸው ቋሚ ጥናቶች አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችን፣ መጠይቆችንና መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣
- ለሚካሄዱት ጥናቶችና ቆጠራዎች አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ማቴሪያሎች የሚገኙበትንና የሚሟሉበትን መንገድ በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በየጥናት ዓይነቶች ላይ የሚሳተፉትን የመረጃ ሰብሳቢዎች፣ የተቆጣጣሪዎችና የሌሎች ባለሙያዎችን ብዛትና የሚገኙበትን ሁኔታ መወሰን፣ ስለምልመላና ሥልጠና ዝግጅት ማጠናቀቅ፡፡

የ1983 ዕቅድ በፕሮግራሙ ቅደም ተከተል መሠረት ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ዘጠኝ ወራት የተገባደዱ ሲሆን የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 3. የ1983 የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን ግምገማ፣

የ1983 ዕቅድ ተግባራዊ መሆን የጀመረው ከሐምሌ 1 ቀን 1982 ጀምሮ ሲሆን የዘጠኝ ወራት ማለትም እስከ መጋቢት 30/1983 ድረስ የተከናወኑትን የስታትስቲክስ ሥራዎች በጥናቶች ዓይነት፣ የበጀትና የሰው ሃይል አጠቃቀም እንደዚሁም ደግሞ በአፈጻጸሙ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 3.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ በሚመለከት የተከናወነ፣

ባለሥልጣኑ የሚያካሂዳቸው ስታትስቲካዊ ጥናቶች በሁለት ዓይነት ዘዴ ተከፍለው የሚካሄዱ ሲሆን አንደኛው በተቀናጀ የገጠር ሰርቬይ ፕሮግራም አማካይነት የሚካሄዱ ጥናቶች ሲሆኑ እነሱም፡ —

ሀ. የሰብል ትንበያ ጥናት
ለ. የእርሻ ናሙና ጥናትና
ሐ. የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ናቸው፡፡

3.2.1 የግብርና ስታትስቲክስ ጥናቶች፡

3.2.1.1 የ1981 የግብርና ናሙና ጥናት አጠቃላይ መረጃ /የግል፣ የመንግሥትና የሕብረት ኣርሻዎች / የያዘ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

3.2.1.2 የ1979ና የ1980 እንዲሁም የ1981 የቤት እንስሳት ብዛት በዓይነት፣ በጾታና በዕድሜ /ለግል፣ ለአምራቾችና ለመንግሥት / የያዙ ሪፖርቶች ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።
የዚሁ ጥናት የ1982 ሪፖርት ዝግጅት ለግልና ለመንግሥት ይዞታዎች ተጠናቆ በግምገማ ላይ ሲሆን የመንግሥት እርሻን በተመለከተ የቅንብሩ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል።

3.2.1.3 ለ1982 አጠቃላይ ሪፖርት ዝግጅት የሚሆነው የ1982 የአምራቾች የሕብረት ኣርሻዎች የበልግ ወቅት የምርትና የታረሰው መሬት ስፋትና የመንግሥት ኣርሻዎች የዋናው መኸር መረጃ በመምሪያው ባለሙያዎች በ"ፒሲ" ተቀነባብሮ ሪፖርቱ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

3.2.1.4 በ "FOOD INFORMATION SYSTEM" ፕሮጀክት አማካይነት ከተለያዩ መ/ቤቶች የሚሰበሰበው መረጃ እንደቀጠለ ሲሆን በሰብል ትንበያ ጥናት " የሰብል ሁኔታ" መረጃ በመጠቀም ሪፖርቱ በኅዳር ወር 1983 ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

3.2.1.5 የ1980 የበልግ ወቅት ምርት ሪፖርት ለአምራቾችና ለሕብረት ሥራ ማኅበራት እንደዚሁም ደግሞ የ1981 የግል ባለይዞታዎች ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

3.2.1.6 የ1983 ሰብል ዘመን የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

3.2.1.7 የ1982 የታረሠ መሬትና የምርት መጠን የያዘ አጠቃላይ ሪፖርት /የግል፣ የአምራቾችና የመንግሥት/ በአብዛኛው ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን የትየባ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡

.../9

3.2.1.8 ለግብርና ናሙና ጥናት የሚያገለግል የአካባቢ የመሬት ስፋት፣
የምርት፣ የሰብል...ወዘተ ኮዱ ቡክ በአማርኛና በእንግሊዝኛ
የተዘጋጀ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለ1983 ግብርና ናሙና
ጥናት የሚያገለግል የኤዲቲንግ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለኤዲተሮች
ተሰራጭቷል።

— "METRIC EQUIVALENT OF AREA LOCAL UNITS".
በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሪፖርት በመገምገም ላይ ሲሆን የሰብል
ዘመንን /CROP CALENDAR/ የሚያሳይ አጠቃላይ ሠን
ጠረዥ በ1983 የተሰበሰበ መረጃን በመጠቀም የቅንብር ሥራ
የተጠናቀቀ ሲሆን ለሕትመት አስፈላጊው ዝግጅት በመደረግ ላይ
ነው።

— የ1981 የትንተና ሠንጠረዥ /CROSS TABULATION/
የሆነ የመሬት አጠቃቀም /LAND UTILIZATION/ የመጀመ
ሪያ ደረጃ ሠንጠረዥ ከተገመገመ በኋላ በመረጃ ማቀነባበሪያ ኣር
ማት በመደረግ ላይ ይገኛል።

3.2.2 <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችና የኤሌትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናት፣</u>

የዚህ ጥናት የ1980 ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ
ሲሆን የ1981 መረጃ ግን የትንተና ሥራ ተጠናቆ የትየባ ሥራ
በመከናወን ላይ ይገኛል። ኤሌትሪክን አስመልክቶ ለመብራት
ሃይል ባለሥልጣን የተላከው የ1981 መጠይቅ ተሞልቶ እንዲላክ
ለን በተደጋጋሚ ቢጠየቅም መጠይቁን በወቅቱ ለመመለስ አልተባበ
ሩም።

3.2.3 <u>ዓመታዊ የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት፣</u>

ለ1980 የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት ዝግጅት የተሰበሰበው
መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። የዚሁ ጥናት
የ1981 መረጃ ተቀነባብሮ የትየባ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

3.2.4 <u>የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፤</u>

3.2.4.1 የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ /PRICE INDEX/ ሥራ ወቅቱን ጠብቆ በየወሩ እየተዘጋጀ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል።

3.2.4.2 <u>በገጠር የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፤</u>

የዚህ ጥናት የ1980 ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። የ1981 የአምራች ዋጋ መረጃ የትንተና ተገባር በመከናወን ላይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የ1982 መረጃ የኤዲቲንግ፤ የኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ተግባር በመጠናቀቅ ላይ ነው።

3.2.4.3 የ1981/82 የ23 ከተሞች የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል። የእነዚሁ ከተሞች የ1982 የዋጋዎች መረጃ ሪፖርት የመተየብ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

3.2.4.4 በተመረጡ 23 ከተሞች የሚካሄደው የሆቴሎች፤ የሕንጻና የምግብ ዋጋ ጥናት የ1981/82 መረጃ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ሆኗል። የእነዚሁ ከተሞች የ1982 በጀት ዓመት መረጃ ቅንበር እየተካሄደ ነው።

3.2.5 <u>የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ፤</u>

3.2.5.1 በ1976 በተካሄደው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የተሰበሰበው መረጃ የትንተና ሪፖርት የማዘጋጀት ተግባር ቀጥሎ በመከናወን ላይ ይገኛል። ቀደም ሲልም በክፍለ ሀገር ደረጃ ከወጡት ሪፖርቶች በተጨማሪ የጎንደርና የወሎ ተጠናቆ የታተመ ሲሆን የትግራይ፤ የኤርትራ፤ የአሰብ አስተዳደርና በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይ ለ1983 በጀት ዓመት የተፈቀደው በጀት ከ1982 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር መደበኛ በጀት በብር 65,432 /2.3% / ዕድገት ሲያሳይ የካፒታል በጀት ግን በብር 980,900 /15.8% / ቀንሷል:: በተጨማሪም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመ/ቤቱ ገቢ መሆን ከነበረበት ገንዘብ ውስጥ ብር 396,796 / 15% / በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀንሶ ቀርቷል:: ይህም በፕሮጀክቱ የሥራ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ መገመት አያዳግትም ከመንግሥት ከተፈቀደው ሌላ ለተለያዩ ጥናቶች ማስፈፀሚያ ብር 517,109.70 ተገኝቷል:: ይኸውም ብር 76,210 ከዓለም አቀፍ የሕፃናት ፈንድ /ዩ.ኒ.ሴ.ፍ/፣ ብር 217,757.60 ከሲዊድን ዓለም አቀፍ ድርጅት /ሲዳ/፣ ብር 173,142.10 ከዓለም አቀፍ የሕዝብ ጥናት ፈንድ/ዩ.ኤን.ኤፍ.ፒ.ኤ / የተገኘ ሲሆን ብር 50,000 ከዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት ሥራ ማስኬጃ የተገኘ ነው::

4.2 የሰው ኃይል አጠቃቀም፣

በዕቅዱ ዓመት መጀመሪያና በዘጠኝ ወር መጨረሻ የነበረው የሰው ሃይል ብዛት ቀጥሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል::

የሰው ኃይል በቅጥርዓይነት

| አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | ጠቅላላ የሠራተኞች ብዛት |
|---|---|---|---|
| | ቋሚ | ኮንትራት | |
| በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበረ | 403 | 1394 | 1797 |
| አዲስ የተቀጠረ | 26 | 34 | 60 |
| በጡረታ የተገለሉ | 1 | — | 1 |
| በሞት የተለዩ | 1 | — | 1 |
| በገዛ ፈቃዳቸው የተሰናበቱ | 13 | 13 | 26 |
| መጋቢት 30 /1983 የነበረ | 414 | 1415 | 1829 |

... /18

በመ/ቤቱ አማካይነት የሚካሄዱት ጥናቶችና የስታቲስቲክስ ሥራዎች በየአስተዳደር አካባቢዎች ደረጃም በመሆኑ ለደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የሚውለው ገንዘብ በባንክ በኩል አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መ/ቤት ይሠራጫል። የሥራው ዐበይ በሰኔ 30 የማይቋረጥ በመሆኑና በተለያዩ ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የወጪ ማስረጃዎች ተጠቃለው ስለማይመጡና ስለማይወራረዱ ሰነዶች በፈሰስ እዳነት ተቆጥረው ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ሂሣብ ተቀናሽ ስለሚደረግ የዕቅዱ ዘመኑን ሥራ በሚገባ ለማንቀሣቀስ አስቸጋሪ ሆኗል። እንደዚሁም የተለያዩ ግለሰቦች በኋላፊነት ካንቀሳቀሱት ገንዘብ በጉድለት የሚፈለግባቸው የሰነድ ሂሣብ መ/ቤቱ በተመሣሣይ ሁኔታ በዕዳ በየጊዜው ይጠየቅበታል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በፕሮጀክቶች ሥራ ማስኬጃ በልዩ ልዩ አርዕስት የተፈቀደው በጀት በየወሩ ሲጠየቅ እየተቀነሰ ስለሚከፈል በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ችግር አስከትሏል። ሆኖም በፕሮግራሙ መሠረት የተፈቀደው በጀት ዘግይቶም ቢሆን ተሟልቶ ይሰጣል በሚል ግምት በመ/ቤቱ ካዝና ከሚገኝ ማናቸውም ገንዘብ ላይ ክፍያ እንዲፈፀም ሁኔታው ያስገድዳል። በመጨረሻም በወጪ አርዕስት ለማስተካከል ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው ገንዘብ ሲጠየቅ ክፍያው የተፈፀመው ለአርዕስቱ ከተያዘው የበጀት ጣሪያ በላይ ያለመሆኑ እየታወቀ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ከመጣው በላይ ተከፍሏል እየተባለ በየዓመቱ ፈሰስ እንጠየቅበታለን። ችግሩም ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸጋገረና እየተደራረበ በየዓመቱ አዳዲስ የፈሰስ ዕዳ እዳታ ከለበት በመሄዱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።